# "ወያኔያዊ አይሲስ"

የጐንቻው!

አርባ ዓመት ሸፍቶ የወረረን ጥልመት፤

አሳር አቆራኝቶ የሚወጋን ባጥንት፤

ከሰይፍ የከፋ 'በሙት ዓጽም' ጉልጥምት፤

ሸል እየከፈለ እያብጠለጠለ እየቆረጠ እትብት፤

ሃገር ሰው ያመከናል እናትን ልጅ ነሳቷት፤

**ጥለቷን አጥቁሮ ግማዷን ደርቦ ነጠላ አለበሳት።**

ሸፍታው የአይሲስ ሞግሸ ወያነ ኃርነት፤
**በአገረ–ሰብ ጩቤ ፋሺስትና ባንዳ እንደገዘዟት፤**
ዶማዎች ተ/አጣርሰው አንገቷን ቆረጧት፤
አካሏን በቅርጫ በክልል በልቷት፤
'ቀይ አበላ' አፍሰው ደም ባህር አስጠሟት።

ሸብር የወለደው ተረግዞ በክፍት፤
'በደም የታረሰው' አጥፍቶ በመጥፋት፤
ድሆ ዳዴ ብሎ እናቱን ላይጦራት፤
የእንግዴ ልጅ ሆነ አድጐ ጡት ነከሳት፤
ወያኔያዊ አይሲስ ኢትዮጵያን አግቷት፤

ሕዝቧ ደጅ ይጠናል ቤቱን ወርሶት ጠላት፤

ሃያ ዓመት ምርኮኛ ባገሩ ላይ ግዞት፤

አሳር ምድር እንጂ ጠበቃ ዋስ የላት፤

ይግባኝ እድሜ ልኳን ዓለም እንዳልሰማት፤

ዘመን ስታንቃቃ በጋው አልፎ ክረምት፤

**ማዕበል ታጎርፍ ይሆን አገር በእስር ሙላት።**

በእትብቷ ገንዞ ፍጥኝ ያሳሰራት፤
ክብሯን የሚያጎድፍ ምትሃት ያደ'ራባት፤
ሰንደቅ እምብርቷ ላይ 'ድፎሽ' አጥሎባት፤
እርሟን እየበላ በከርሱ ከረጢት፤
እድፍ ጉድፍ ቃርሞ እንደ ጨርቅ ቋጠራት፤
ሲያሻው መለመኛ አስይዞ ቅኝ ግዛት፤
**ለባዕድ 'አገልግሏ' ለዜጎቿ አልቦ ናት፤**
**ለነጭ እጅ መንሻ ጥቁር ሰይጣን ጥሏት።**
















የኢትዮጵያና የሕዝቧ አምላክ የእጃችሁን በእጥፉ ይስጣቹህ !!!

ልጅ አባቱን ተካ ሹምባሽ ውጭ ሹመኛ፤
አገር ሃራጅ ሽጦ አይን አውጣ ሙሰኛ፤
ያገር - ሕዝብ ካዝና ዘርፎ በላተኛ፤
ዶላር በቢሊዬን 'ግብር አቅፎ እሚተኛ'፤
'የነጭ ደመላሽ' 'ጥቁር - በቀለኛ፤
መቶ ሚሊየን አስሮ 'መንግስት ሆነ ዳኛ'፤
ወያኔያዊ አይሲስ 'የአበሻ መጋኛ'፤
**በሽብር ይከብራል እዳ አውርሶን ለኛ።**

የጥቁር ሕዝብ ክብር በዓለም አሳነሰ፤
የባንዳ ልጅ ሎሌ ቅኝ እያወደሰ፤
በሮም ተደገሰ፤ ለንደን ተደነሰ፤
ዋሺንግተን ዲሲ ዶላር ገፍ ታፈሰ፤
በአበሻ ምድርማ እዝን ተለቀሰ፤
በመከራ ጎጀው የፈራው ደረሰ፤
ሽፍታው ለምድ ለብሶ ዙፋኑን ወረሰ፤
ወያኔው ገዘፈ አገሬው ኮሰሰ፤
አጋዚ አሰማርቶ ባገር በመዲና ደም እያፈሰሰ፤
**ማህጸን ረግጦ ጽንስ <u>የሚጋረፍ</u> ከፋሺስት የባሰ፤**
እጆቿን ዘርግታ ቃል ኪዳኗ ሰምሮ እንደተመለሰ፤
እንዳመጣጣቸው አግዞ አጋግዞ እያግበሰበሰ፤
**ይውሰድልን ወሳጅ ያምናና ታቻምናው ጥንድ ቆሪጥ ያፈሰ።**

yegonchaw@yahoo.co.uk 26.01.2015

**<u>ማስታዋሻ</u>፡-**

<u>በቅድሚያ በዓረመኔው ወያኔ ቅልብ አጋዚ ድብደባ የመከራ ገፈታ ቀማሽ ለሆኑት ቆራጥ የነፃነት ታጋዮችና በእናቱ ማህጸን ውስጥ ሆኖ/ና በሽፍቶች በትር ለተጎዳች/ው ጽንስ እንደ ፈጣሪ ቸርነት በሰላምና ጤና ተወልዶ/ዳ የጀግና እናቱን/ቷንና የራሱ/ሷንም ኩሩ ኢትዮጵያዊ ገድል ይ/ትቀጥል ዘንድ እየተመኘሁ፤ በዓራዓያነቱ ደግሞ ሁላችንም የተቀጣጠለው ትግል እስከነፃነትና ድል ድረስ በቆራጥነት እንድቀጥል።</u>